ትራንስ ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ ማህበር ባዘጋጀው ስፔስፊኬሽን መስረት የተለያዩ የአትሌቲክስ የስፖርት ትጥቆች እና ተዛማጅ ዕቃዎች በጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል::ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መስፈርቶች በማሟላት በጨረታው እድትሳተፉ ይጋብዛል:

- የተለቀቀበት ቀን: ረቡዕ ሕዳር 1, 2008 (ከ 11 ዓመታት)
- መዝግያ ቀን: ሕዳር 18, 2008 6:00 ከሰአት (ተዘጋ)
- የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:
- ቦታ:መቐለ
- የጨረታ ደኩመንት ዋጋ:50
- ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: ሕዳር 18, 2008 6:00 ከሰአት
- ምድብ: ናይ ስፖርት ዕጥቅን ተዛመድቲ አቁሑትን/

- በዚህ የስራ መስክ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑ ግብር የከፈሉ መሆን አለባቸው (የማስረጃው ፎቶ ኮፒ ማያያዝ ያስፈልጋል)
- ተጫራቾች ለእያንዳንዱ ዕቃ የጨረታ ዋጋ ሲያስገቡ በጨረታ ሰነዱ በተገለፀው ስፔስፊኬሽን መሆን አለበት፣ከስፔስፊኬሽን ውጭ ያቀረበ ተቀባይነት አይኖረውም፣
- ተጫራቶች የጨረታ ዋጋቸው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚጨምርና የማይጨምር መሆኑ በግልፅ ማስቀመጥ አለባቸው፣ካልገለፁ የጨረታ ዋጋው የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዳካተተ ይቆጠራል::
- የጨረታው አሸናፊ ጨረታው አሸናፊ መሆኑ ከተገለፀለት ቀን ጀምሮ ያሸነፋቸው ዕቃዎች በ15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ መቀሌ በሚገኘው ስቶራችን በራሱ ትራንስፖርት በማጓጓዝ ማስረከብ አለበት::
- ተጫራቾች ላሸነፉበት ገንዘብ ክፍያ የሚፈፀምላቸው ያሸነፉት ዕቃ ኢንስፔክት ተደርጎ የገቢ ደረስኝ ከተቆረጠለት በኃላ መሆኑ ተጫራቾች አስቀድመው ማወቅ አለባቸው::
- የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ የማይመለስ ብር 50 /አምሳ ብር/ በመክፈል ከመቀሌ ዋና መ/ቤት ከግዢ፣ ንብረት አቅርቦትና ቁጥጥር መምሪያ ቢሮ ወይም ከአዲስ አበባ ላይዘን ኦፊስ ግዢ ማስተባበሪያ በድሉ ሕንፃ በስራ ስዓት መውሰድ ይችላሉ፣
- የጨረታ ማስከበሪያ ከጠቅላላ ያስገቡት ዋጋ 2% በትራንስ ኢትዮጵያ ኃ.የተ.የግ ማህበር ሰም በሲፕኦ (CPO) መልክ ማስያዝ ይኖርባቸዋል::ሲፒኦ ያላስያዘ ተጫራች ወድያው ከጨረታ ይሰረዛል፣
- ተጫራቾች በተሰጣቸው ሰነድ ውስጥ ብቻ ዋጋቸውን ሞልተው በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ እስከ ሕዳር 18 ቀን 2008 ዓ.ም ከጥዋቱ 4፡00 ባለው ጊዜ ውስጥ በአዲስ አበባ ላይዘን ኦፊስ ግዢ ማስተባበሪያ በድሉ ሕንፃ ወይም መቀሌ በሚገኘው የግዢ፣ ንብረት አቅርቦትና ቁጥጥር መምሪያ ቢሮ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው::
- በጨረታ ሰነዱ የተቀመጠ ቁጥርም በPO ጊዜ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፣
- ጨረታው በዚሁ ቀን ማለትም ሕዳር 18 ቀን 2008 ዓ.ም ዓ.ም ከረፋዱ 4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በመቀሌ ዋና መ/ቤት በትንሿ አደራሽ እና በአዲስ አበባ ላይዘን ኦፊስ ግዢ ማስተባበሪያ በድሉ ሕንፃ በተመሳሳይ ስዓት ይከፈታል:: በዕለቱ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው ባይገኙም የጨረታ ሰነዱ የተሟላ ከሆነ ጨረታው በተጠቀሰው ሰዓት ይከፈታል::
- ኩባንያው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታው በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

ተጨማሪ ማብራርያ ካስፈለገ በስልክ ቁጥር 034-441 64 39 / 034-440 82 05 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ::